# ብ/ጀኔራል ታዬ ጥላሁን - አምስተኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ

(ከ1969 -

ምንጭ - የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ መፅሃፍ (1921 -1983)



ጀ/ል ታዬ ጥላሁን በ1924 ዓም ሆሳዕና ከተማ ተወለዱ ። በአራት ዓመታቸው ጣልያን ኢትዮጵያን በመውረሯ አባታቸው አቶ መኰንን ጠላትን በመከላከል ላይ እንዳሉ ወጥተው ሳይመለሱ ቀሩ ። በዚህ ምክንያት ከልጅነታቸው ጀምሮ ከእናታቸውና ከእንጀራ አባታቸው ከአቶ ጥላሁን ጋር ያደጉ ሰው ናቸው ። እናታቸው በባለቤታቸው ሞት ምክንያት እጅግ ከማዘናቸውም በላይ ኑሮውም ስለከበዳቸው ወጣቱን ልጃቸውን ታዬን ይዘው ከሆሳዕና ወደ አዲስ አበባ መጡ ።

ወጣት ታዬ በአጋጣሚ አገር አስተዳደር ሚኒስቴር ግቢ ውስጥ ለአንድ የዕርዳታ ድርጅት ከሚሰሩ ማውንሲ ኤድዋርድ ሪቲ (Mounsey Edward Rithey) ከተባሉ የእንግሊዝ ተወላጅ ከሆኑ ሰው ጋር ይገናኝና ሚስተር ሪቲ ታዬን ትምህርት ለማስተማር ወስነው ከታዬ እናት ጋር ይነጋገራሉ ። ይህ አጋጣሚ የወጣት ታዬን የወደፊት ሕይወት ግዙፍ በሆነ መልኩ የቀየሰ ይሆናል ። ማውንሴ ለወጣት ታዬ የነበራቸው ግብ እንግሊዘኛ ቋንቋ በደንብ ተምሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ እንግሊዝ አገር ሄዶ እንዲማርና ተመልሶ አገሩን በከፍተኛ ደረጃ ማገልገል እንዲችል ነበር ። በዚህ ዕቅድ መሰረት ዛሬ ሊሴ ገብረማርያም ያን ጊዜ ግን አርበኞች ትምህርት ቤት በሚባለው ትምህርት ቤት እንዲገባ አድረጉ ።

በመሐሉ ሚስተር ሪቲንና ድርጅቱ ውስጥ የነበሩትን የውጭ ዜጐች መንግስት ሰላዮች ናቸው ብሎ ከአገር እንዲወጡ ስላደረገ ሪቲ አገር ለቀው ከመውጣታቸው በፊት በነበራቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ የወጣት ታዬን የወደፊት ሁኔታ ለማስተካከል ይሞክራሉ ። መኪናቸውን ሸጠው በተገኘው ገንዘብ ታዬን ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በአዳሪነት ከፍለው እንዲገባ አድረጉ ። አባታዊ ምክር በመስጠት ታዬ ትምህርቱን ተግቶ እንዲማር አደራ ጥለውበት ሄዱ ። ይሁን እንጂ ወጣት ታዬ ሚስተር ሪቲ የጣለበትን አደራ ቀስ በቀስ መዘንጋት ጀመረ ። የአየር ኃይል መኰንኖች ትምህርት ቤት ድረስ እየሄዱ እጩ መኰንኖችን ይመለምሉ ስለነበር ታዬ ለኒያ ደግ ሰው ለሪቲ ምንም ፍንጭ ሳይሰጥ አየር ኃይል በመቀጠር ትምህርቱን አቋረጠ ። አዛኝ ወዳጃቸውን ሳያማክሩ አየር ኃይል ለመግባት መወሰናቸው ጀ/ል ታዬን አሁን ድረስ እጅግ ይፀፅታቸዋል ። ምክንያቱም ሪቲ ያቀዱላቸው ሌላ ስለነበር ነው ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በኢትዮጵያ አየር ኃይል ለአውሮፕላን አብራሪነት በ 1940 ዓም ተቀጠሩ ። የክፍል ትምህርቱንና የበረራ ሥልጠናውን በሚገባ ካጠናቀቁ በኋላ የምክትል መ/አለቅነት ማዕረግ በ1944 ዓም አገኙ ። በማዕረግና በኃላፊነት በፍጥነት እያደጉ ከመጡት በመጀመሪያዎቹ የአየር ኃይል ዓመታት ከተቀጠሩት ወጣቶች መካከል ታዬ አንዱ ስለነበሩ በ 1950 ዓም  የመጀመሪያው የዘመናዊ የአየር ኃይል ኢትዮጵያዊ የበረራ ትምህርት ቤት አዛዥ በመሆን ከስዊድናዊው አዛዥ ለመረከብ ቻሉ ። ከዚያም የበረራ አስተማሪዎቹም በሙሉ ኢትዮጵያውያን እንዲሆኑ ለማድረግ ችለዋል ።
ጀ/ል ታዬ ገና ሻምበል እያሉ ሲስተር ራሄል ፀጋዬን አግብተው የሶስት ልጆች አባት ናቸው ። አየር ኃይል ውስጥ በማዕረግ እያደጉ ከስኳድሮን አዛዥነት እስከ ምድብ አዛዥነትና በመጨረሻም የአየር ኃይል አዛዥ በመሆን ከፍተኛ የአመራር ብቃትና ውጤት ያሳዩ መኰንን ናቸው ።



ሶማልያ ኢትዮጵያን በ 1969 ዓም ስትወር የአየር ኃይል አዛዥ ሆነው ወራሪው ጦር በመጣበት እግሩ ተዋርዶ ወደ አገሩ እንዲመለስ በተደረገው ትግል የአየር ኃይሉን ትልቅ ድርሻ የመሩ ከፍተኛ የአገር ፍቅር ያላቸው የሕዝብ ወገናዊነታቸው የሚደነቅ አየር ኃይል የሚኰራባቸው ጀነራል መኰንን ናቸው ። የአየር ኃይል ተሳትፎ የሰራዊቱ እንደ አንድ ሰው ተባብሮ የአገርን ዳር ድንበር ለመጠበቅ የተደረገ ትግል ውጤት ነው ቢባልም የጀ/ል ታዬ የወቅቱ አመራር ወሳኝነት ነበረው ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጀ/ል ታዬ ለአገራቸው ያላቸውን ከፍተኛ ፍቅር የእያንዳንዱ ዘማች ችግር በቅርብ እየተገኙ ለመረዳት በመሞከርና መፍትሄ በመፈለግ አየር ኃይሉን ጠንካራ የአገር ዳር ድንበርና አንድነት ዘበኛ እንዲሆን በተለይ በጦርነቱ ወቅት ብዙ ጥረቶች አድርገዋል ። በእንደዚያ ዓይነት ቀውጢ ጊዜ ውሳኔዎች በትዕግስትና በአርቆ አስተዋይነት ሲመሰረቱ ውጤቱ የዚያን ያህል አመርቂ ይሆናል ። ጀ/ሉ ስለ ሶማልያ ጦርነት ቃለ ሕይወት ለተባልው መፅሄት በሰጡት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት " በሶማልያው ጦርነት የአየር ኃይሉ ሚና በእጅጉ የሚያኲራ ነበር ። እንዴት ዓይነት አስደናቂ በራሪዎች የተወለዱበት ታሪካዊ ወቅት እንደነበር ለመግለፅ ቃላት ያጥረኛል ። የሙያ ክብር በፖለቲካ አቋም ምክንያት የሶማሊያ ወረራ የተቋቋመው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ሁሉም የጦር ክፍል ቢሆንም የአየር ኃይሉ ድርሻ ግን እጅግ ከፍተኛ እንደነበር ማስታወስ እወዳለሁ ። በዙሪያዬ የነበሩት ታላላቅ መኰንኖችና የአየር ኃይሉ ባልደረቦች ኃአፊነታቸውን ለመወጣት ያደረጉት ትግል ፣ የነበረውን ትጋትና ቁርጠኝነት በፍፁም አልረሳውም ።



ጀ/ል ታዬ አየር ኃይል ያሳዩት ብቃትና ውጤት ምስክር ሆኖ ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እየተዘዋወሩ በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች እየተመደቡ አገራቸውን በቅንነት አገልግለዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

- ከአየር ኃይል ወደ ባሕር ኃይል ተዛውረው የባሕር ኃይል ኤታ ማዦር ሹም በመሆን አገልግለዋል ።
- ከባሕር ኃይል ተቀይረው የአየር ኃይል አዛዥና
- ቀጥለውም የአገር መከላከያ መኒስትርና ከዚያም የአገር አስተዳደር ሚኒስትር

ሆነው አገልግለዋል ።




ዓመታት አልፈው ጀነራል ታዬ መኪና የጠበቁበትን ግቢ የተመኙት በእንደዚህ ያለ ከፍተኛ ኃላፊነት አገርን ማገልገል ስለነበር ምኞታቸው ተሳክቷል ማለት ይቻላል ። ጀ/ል ታዬ ይህንን አጋጣሚ ሲገልፁት " መቼም የእግዚአብሔር የረቀቀ ዕቅድ ለመረዳት አዳጋች ቢሆንም በእኔ ሕይወት ግን የነበረው ልዩ ዓላማ የሚያስደንቅ ነበር ። ያን ጊዜ መኪና እጠብቅበት ለነበረው የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር በኋላ ሚኒስትር እንደምሆን ከእግዚአብሔር በቀር ማን ያውቅ ነበር ?" ብለዋል ። እውነትም የሚያስደንቅ አጋጣሚ ነው ።

ከአገር አስተዳደር ተነስተው በውጭ አገ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ሰርተዋል ። ይህ የአምባሳደርነት ሹመት የተሰጣቸው አገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉ የገኙው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ፓርቲ አባል መሆን አለባቸው የሚል አንድ መመሪያ ወጥቶ በዚያ ትዕዛዝ መሰረት ሚኒስትር ስለነበሩ የፓርቲ አባል እንዲሆኑ መጠየቃቸውን ተከትሎ ነው ። ጀ/ል ታዬ ፍላጐቱ ስላልነበራቸው ጥያቄውን አልተቀበሉም ። በወዳጅ ዘመድ አባል እንዲሆኑ ከመመከራቸውም በላይ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም እራሳቸው ቢሮዋቸው ጠርተው “እንግዲህ እርሶ በሚገባ እንደሚያውቁት በከፍተኛ የመንግስት ኃላፊነት ላይ የሚቀመጥ ሰው የፓርቲ አባል መሆን ይኖርበታል የሚል ደንብ አለን ፤ እርስዎ ደግሞ በፓርቲ አባልነት ጉዳይ ላይ እንደማይስማሙ ጓደኞችዎ ነግረውኛል ፤ ዛሬ እኔ እንዲጠሩ ያደረግሆት ከራስዎ አንደበት ልስማ ብዮ ነው “ አሏቸው ። ጀ/ል ታዬ ለፕሬዝዳንቱ የሰጡት መልስ “ ጓድ ሊቅመንበር ስለተደረገልኝ መልካም ነገር ሁሉ አመሰግናለሁ ፤ እርግጥ ነው እኔ በእግዚአብሔር ፅኑ እምነት አለኝ ፤ መንግስታትን ሁሉ ወደ ሥልጣን የሚያመጣው እግዚአብሔር እንደሆነ አምናለሁ ። ይህንን መንግስትም እግዚአብሔር እንዳመጣው አምናለሁ ። የፖለቲካ አባል ለመሆን ፈቃዴ አይደለም ፤ አገሬ አገልግሎት የምትፈልግ ከሆነ የትም ልትመድቡኝ ትችላላችሁ ። ከዚህ በተረፈ ግን ለእናንተ አሰራር የማልመች ከሆነ በክብር አሰናብቱኝ ፤ የሚል ነበር ። ሊቀመንበሩ በረጋ ስሜትና በአክብሮት “ ሃሳብዎን በግልፅ ስለነገሩኝ አመሰግናለሁ ። ዕድሜዎና ጤንነትዎ እስከፈቀደ ድረስ አገርዎን ከማገልገል የሚከለክልዎት የለም” ብለው ሸኟቸው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በስዊድን የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው ተሾሙ ።



ጀ/ል ታዬ አምባሳደር ሆነው ብዙ ሳይቆዩ ሥራውንም ሆነ ሕይወቱን በአጠቃላይ ሕሊናቸው ሊቀበለው አልቻለም ፤ ምክንያቱም የኰሚውኒዝም የፖለቲካ አቅጣጫና የክርስትና ሕይወታቸው

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ግጭት እየፈጠረ በጣም በመቸገራቸው ነው ። በተጨማሪም መንግስት ሲዋሽ መዋሸት ፣ ማስተባበያ ሲሰጥ ዋሽቶ ማስተባበያውን ማጋነን የሥራው ጠባይ ይፈልግ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ ክርስትያን ነኝ ብለው ጠዋትና ማታ ፀሎት ቤት ከቤተሰባቸው ጋር ይሄዱ ስለነበር ይህን ሁለት ተቃራኒ ነገር ማስታረቅ አልቻሉም ነበር ። ስለዚህ ለዚህ ችግራቸው መፍትሔ ለማበጀት ከቤተሰብ ጋር ጊዜ ወስደው ከተማከሩ በኋላ በተመደቡበት ሥራ ከመንግስት ጋር መቀጠል እንደማይችሉ ማሳወቁን መረጡ ። ይህ ምርጫመው የተመሰረተው “ ክርስትናና በአንድ መንግስት የፖለቲካ ሥርዓት ሁልጊዜም ሊጣጣሙ አይችሉም ከሚል አይደለም ። ጀ/ል ታዬ እንደሚሉት ለውሳኔያቸው ዋናው ምክንያት “ ፖለቲካው የክርስትና እምነታቸውን ተጭኖ እርሱ ጌታ ፣ እምነታቸው ሎሌ መሆን ስለጀመረ ነው” ይላሉ ። ቀጥለውም “ የአገርም መሪ ሆንን ሚኒስትር ዝቅ ብለን ሕዝቡን ለማገልገል አደራ አለብን ። መሪ የሕዝብ አገልጋይ ነው ። በለሥልጣን መሆን እኮ ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል መሆን አለበት ። ምንግስትን ወደ ዙፋን የሚያመጣው እግዚአብሔር ከሆነ ከዙፋኑም ላይ ጥሎ ማውረድ አያቅተውም ። መሪዎቻችን ፈሪሃ እግዚአብሔር ካላቸው ሕዝብ በሰላም ይኖራል ። መሪዎች በፈጣሪ ላይ ማመፅ ሲጀምሩ ግን ሕዝብን በእነርሱ ላይ አነሳስቶ ይቀጣቸዋል ። የእኔም ችግር ሕዝብን ማገልገሉ ላይ ሳይሆን አምላኬን ለመካድና ለማዋረድ ስላልፈቀድኩ ሥራውን ለመልቀቅ እርምጃ እንድወስድ ተገደድኩ” ይላሉ ።

ጀ/ል ታዬ ክርስቲያን በመሆናቸው የደርግ አባሎች በሃይማኖታቸው ምክንያት እሳቸውን የጦር መሪ ማድረግ ያሰጋቸው እንደነበረና ጀ/ሉ ግን በማንም ሰው ፊት “በሃገሬ ጉዳይ ላይ አልደራደርም ፤ ለሃገሬ ክብርና ነፃነት እስከመጨረሻው እዋደቃለሁ” በማለት በይፋ ይናገሩም ይከራከሩም ነበር ። “እባካችሁ እናንተ ካላስቸገራችሁኝ በስተቀር እምነቴና የሃገሬ ጉዳይ አይጋጩብኝም” … ክርስቲያን መሆን ማለት ይበልጥ ለሃገር መቆርቆር ማለት ነው” በማለት ይከራከሩ ነበር ይላሉ መስካሪው ኩ/ል ክፍሌ ስዩም ።

የወቅቱ የኢትዮጵያ መሪ ኩ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም ስለ ጀ/ል ታዬ ከሰቱት ምስክርነት ከፊሉ ..” ታዬ ጥላሁን ለራሳቸው ካላቸው ብቃት ሌላ ሃይማኖተኛ ሰው ናቸው ። እኔ ደግሞ ሰላሳውን ከሚቀባጥ ወሸከሬ ኰሚኒስት ነኝ ባይ ይልቅ በሃይማኖታዊ እምነቱ የፀና ሰው በጣም አከብራለሁ ። የሚያምንበትን ነገር ሳይዋሽ ፊት ለፊት አውጥቶ የሚናገር ሰው ለሌላውም ነገር እምነት ሊጣልበት ይችላል “ ብለዋል ።

የሶማልያ ጦር ድሬዳዋን ለመያዝ ባደረገው ጦርነት ዘመቻውን ሲመሩ የነበሩት ኩ/ል ፋንታ በላይ ሶማሌዎች እንዲሸነፉና በመጡበት እንዲመለሱ ያደረጉትን ጥረት በማድነቅ ይመሰክራሉ ። ጀ/ል ታዬ አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ሆነው ሁኔታው እጅግ አሳሳቢና አደገኛ እየሆነ መምጣቱን ሲረዱ ጣቢያ ውስጥ ያለውን ምስጢር ዶክሜንት አቃጥለው እንዲወጡ ትዕዛዝ ለኩ/ል ፋንታ አልለቅም ማለታቸውና ከዚያ በኋላ የወሰዱትን ጦር የማስተባበርና የመከላከል እርምጃ ጀ/ል ታዬ በማድነቅ ይናገራሉ ። ውጊያው ወደ ድሬዳዋ እየተቃረበ ሲሄድ ድሬዳዋ ጣቢያ የነበረውን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አውሮፕላን ሁሉ መሬት ላይ እንዳሉ እንዳይመቱ እንዲነሱና ከደብረ ዘይት እየተነሱ ድጋፍ እንዲሰጡ አድርገዋል ።

ጀ/ል ፋንታ ደርግን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ይጠሉ የነበረና እየቆየ ሲሄድ ደግሞ ይህ ጥላቻ እየጨመረና ሊቀመንበር መንግስቱን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይደፍሯቸውና ይጋጩ እንደነበር ጀ/ል ታዬ ያስታውሳሉ ። ጀ/ል ፋንታ ይህን ያደርጉ የነበረው የደርግ አሰራር አገሪቱን ይጠቅማል ብለው ካለማመን ብቻ ሳይሆን ፤ ሞክረው ሳይሳካ ቀረ እንጂ መሪነቱን ይዘው የተሻለ ስራ ለመስራት ከመፈለግ ጭምርም ነበር ።

ጀ/ል ታዬ የአየር ኃይል አዛዥ ሆነው በሰሩባቸው 6 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተሳካ ውጤት የተገኘበት ምክንያት አመራራቸው ውስጥ በችሎታቸውና በዕውቀታቸው የተመሰከረላቸው መኰንኖች አብረዋቸው ይሰሩ ስለነበር እንደሆነ ይናገራሉ ። የዘመቻ ፣ የሎጅስቲክስ ፣ የጥገና ፣ የአየር ምድብ አዛዦች ፣ የኰሚኒኬሽንና ሌሎችም ኃላፊዎች ያሳዩት ትብብርና የአገር ፍቅር ከፍተኛ የሥራ ውጤት እንዲገኝና የአየር ኃይል ግዳጅ አፈፃፀም አስደናቂ እንዲሆን አስችለዋል ። የእነዚህ ከፍተኛ የሥራ ውጤት ግኝቶች የሶማልያን ጦርነት በአጭር ጊዜ እንድንወጣው ዋነኛ ምክንያት ነበር ብለዋል ።

አድኃሪያንና ሥራ ችሎታ የሌላቸው ሰዎች መሰናበት አለባቸው እየተባለ ሊስት ከደርግ ይመጣ ነበር ። ሌሎች ኃይሎች እነዚህን የማይጠቅሙና ለአብዮት እንቅፋት ከመሆን የማይቦዝኑ አባሎች ከኃይሎቻቸው አስወጥተዋል ፤ አየር ኃይል ብቻ ነው የቀረው የሚል ጥያቄ ከመንግስት እየመጣ ከፍተኛ ጫና ነበር ። ሰው ዝም ብሎ ማስወጣት አስቸጋሪ ስለሆነ አየር ኃይሉ የሚወጡ ሰዎችን ለመምረጥ መስፈርት ማዘጋጀት ነበረበት ። ይህም ሆኖ አንዱ ከሌላው ይበልጣል በሚል ብቻ የሚፈለጉ መኰንኖችና የበታች ሹሞች እንዳይወጡ ተደርጓል ። ይህ በአብዮት ስም አገሪቱ በሙያቸው ፣ በልምዳቸውና በችሎታቸው እጅግ የምትፈልጋቸው መኰንኖችና የበታች ሹሞች ከአየር ኃይል እንዲሰናበቱ መደረጉ ትክክል እንዳልሆነና እንዳሳዘናቸው ጀ/ል ታዬ በቁጭትና በሐዘን ይገልፃሉ ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com